# አስገራሚ ሰዎች

በጋሻ ቀለሙ

EthioLion.Com

አንዳንድ ሰዉ አለ ፤ ሞትን የማይፈራ
ለሐገሬ ብሎ ፤ በሚሰራው ስራ

አንዳንድ ሰዉ ደግሞ ፤ ፅኑ ነው ባቋሙ
ይከፍላል ለሐገር ፤ በደሙና ባፅሙ

አንዳንድ ሰዉ አለ ፤ በጣም የቀለለ
እድሜ ቀጠረ እንጅ ፤ ሽምግሎ ያልበሰል

አንዳንዱም ሊያስመስል ፤ ባህሉን አክባሪ
በፈረንጆች ሐገር ፤ ሽማ ለብሶ ዟሪ

አንዳንድም ነበረ ፤ ጀግና የማይፈራ
ታሪክ ሰርቶ አላፊ ፤ ወገን የሚያኮራ

አንዳንድ ሰዉ አለ ፤ ተናግሮ አናጋሪ
ጆሮ የሚጠባ ፤ ሆኖ ፊርማቶሪ

አንዳንዱም ሆነና ፤ ወዳጅ ፍርፋሪ
ወገኑን ይሸጣል ፤ ለገዳይ ለአሳሪ

አንዳንድ ሰዉ አለ ፤ ለወገኑ አኩሪ
ሐገሩን ጠባቂ ፤ ድንበሩን አጣሪ

አንዳንዱ ሰዉ ደግሞ ፤ ፈሪ ነዉ ደንባሪ
እራሱን የሚሸጥ ፤ ለባእድ አዳሪ

አንዳንድ ሰዉ አለ ፤ የመድረክ አዋጊ
ብርሃኑን አይቶ ፤ ጨለማን ተጠጊ

አንዳንድ ሰዉ አለ ፤ ጠባብ ብኄርተኛ
ሐገር ለመበተን ፤ ቆሞ የማይተኛ

አንዳንድ ሰዉ አለ ፤ ላዩን እየቃጣ
የሌላዉን ሲያስብ ፤ የራሱን የሚያጣ

አንዳንድ ሰዉ አለ ፤ ሊቅ ተመራማሪ
ዕዉቀቱን አካፋይ ፤ ሕዝብን አስተማሪ

አንዳንድም ሰዉ አለ ፤ በስተርጂናዉ የሚያብድ
መርሻ የሌለዉ ቂም ፤ አስይዞ የሚሄድ

አንዳንዱማ ደግሞ ፤ የክህደት ክብደቱ
ከመወለጃዉ ነዉ ፤ ያዉም ከልደቱ

አንዳንድ ሰዉ አለ ፤ አስቦም ተክዞ
ኃይሉን አጠናክሮ ፤ የሚቀጥል ጉዞ

አንዳንዱም ይሆናል ፤ በዕድሜ የበሰለ
በደምና አጥንቱ ፤ ድርሻ የከፈለ

አንዳንድ ሰዉ አለ ፤ ወሬኛ ለፍላፊ
ጨለማን አቅራቢ ፤ ብርሃን ገፋፊ

አንዳንድ ሰው አለ ፤ አስመሳይ አርበኛ
ሌሊት ከጠላት ቤት ፤ ቀን የሚዉል ከእኛ

አንዳንድም ሰዉ አለ ፤ ተስፋ የቆረጠ
ለቀደመው ሰይጣን ፤ እራሱን የሸጠ

አንዳንዱማ ደግሞ ፤ የዋህ ነዉ ተላላ
ከጠላት ከወዳጅ ፤ አብሮ የሚበላ

አንዳንድ ሰዉ አለ ፤ የሚወድ ጥቅም
ሁሌ የሚጠጋ ፤ እያየ ባለአቅም

አንዳንድም ሰዉ አለ ፤ በዘር የሚነዳ
መንጋየ ከሄደ ፤ ብሎ የሚከዳ

አንዳንድ ሰዉ አለ ፤ አታላይ ቀጣፊ
የአንዱ ወገን መስሎ ፤ የሌላዉ ተለጣፊ

አንዳንድ ሰው አለ ፤ ሐገር የሚሰልል
ዘመኑ ሲለወጥ ፤ ሊሆን መስፍን ልዑል

አንዳንድ ሰዉ ደግሞ ፤ የማያስተዉል ብኩን
ቋንቋዉን ወርዉሮ ፤ ልማር ይላል ላቲን

May 29, 2009

አንዳንድ ሰዉ አለ ፤ ምንም ቢያከብሩት
ሁልጊዜ የሚያስብ ፤ በዝቅተኛነት

አንዳንድ ደግሞ አለ ፤ ትልቅ መሳይ ታናሽ
አዋቂን የሚዘልፍ ፤ በስብሰባ አዳራሽ

አንዳንድ ሰው አለ ፤ ወገን የሚጎዳ
ጊዜው ካሞቀው ጋር ፤ አብሮ የሚነዳ

አንዳንድ አለ ደግሞ ፤ ነገርን ጠርጣሪ
አጣርቶ የሚጓዝ ፤ ሰልፉን አሳማሪ
እናስተዉል ብሎ ፤ ወገኑን መካሪ
ለሐገሩ ጠበቃ ፤ ቋሚ ተከራካሪ

አንዳንድም ሰው አለ ፤ የተነሳ ቆርጦ
ዕዉነትን ሊያወጣ ፤ ቆንጥጦ ወረንጦ

አንዳንድ ሰው አለ ፤ ግፍ መብዛቱን ያየ
የሞላው እስር ቤት ፤ ተከፍቶ በታየ

አንዳንድ ሰዉ አለ ፤ ተዋጊና አርበኛ
ግዳጁን ተወጥቶ ፤ ታየ ቆሞ ለእኛ

አንዳንዱ ሰዉ ደግሞ ፤ አለሁ አለሁ ይላል
ቁርጥ ቀን ሲመጣ ፤ እጅ ሊሰጥ ያስባል

አንዳንድ ሰዉ አለ ፤ በፍጥነት በርጋጊ
የሚያስብ በሩቁ ፤ ሊሆነን አዋጊ

አንዳንድ ሰዉ ደግሞ ፤ ለፍላፊ ወሬኛ
ለጠላት ያደረ ፤ የባንዳ መላክተኛ

ለሌሎችም አዘንኩ ፤ እኔም በመሳሳቴ
ሳላዉቅ ስከተል ፤ በመንከራተቴ
ብዙ ጊዜ አጠፋሁ ፤ በየዋህነቴ
ያለፈው ስህተቴ ፤ ከሆነኝ ትምህርቴ
መፍትሄው ተገኝቷል ፤ ተጽፏል ከፊቴ
ለይቶ ማወቅ ነዉ ፤ ወዳጅን ከጠላቴ

gashakelemu@yahoo.com



Ethiopia will prevail !

EthioLion.Com